# በሰነድ የተደገፈ የመንግሥት ዓይን ያወጣ ዘረፋና ብዝበዛ

ዘረፋ በአንድ ወሮበላ,ሽፍታ ወይም ቡድን የሚፈጸም ወንጀል እንደሆነ ቢታመንም በአገራችን ግን በመንግሥት ደረጃ በየቀኑ የሚከናወን ድርጊት ነው።ከዘረፋው ጎን ለጎንም በቋሚነት በሕግና አንቀጽ ተደግፎ የሚከናወን መንግሥታዊ የብዝበዛ ስርዓት ሰፍኖ ይገኛል።ዘረፋ፣ነጠቃ፣ ወይም ስርቆት (robery)ወንጀል ሆኖ በብዙ አገሮች ሲያስቀጣ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ግን በስርቆቱ የሚሰማሩት ባለሥልጣኖቹ ስለሆኑ የሕግ ሽፋን የያዘ ሕጋዊ ወንጀል ነው። በባለሥልጣኖቹና በውጭና በአገር በቀሎቹ የጥቅም ሸሪኮችና የነዚህ ጥቅም አስከባሪዎች በሚወስዱት ጨካኝ የማጥቃት እርምጃ በመሬት፣በገንዘብ፣በቤትና ንብረት፣ በሠራተኛው ጉልበትና ላብ የሚከናወነው  ዘረፋ፣ ምዝበራና ብዝበዛ፣ ጣራ ላይ ደርሶ ደም ያፋሰሰ ችግር ሆኗል፣ለወደፊቱም ደም ለማፋሰስ የሚችል ስጋት ፈጥሯል።ሰሞኑን በደቾች የአበባ እርሻ ዙሪያ ይፋ የወጣው የምዝበራ ክንውን ቀደም ሲልም በደቾች የሃይነከን ቢራ ፋብሪካ፣በቻይናዎች የጫማ ፋብሪካና በስዊድኖች የልብስ ፋብሪካ የሚካሄደው ዘረፋና የማጋለጥ እርምጃ የዚሁ የብዝበዛ ሰንሰለት አካል ነው።በፋብሪካዎችና በእርሻ ልማት ዙሪያ ከሚካሄደው ምዝበራ ባላነሰ ደረጃ የሚከናወነው ሌላው የዘረፋ መስክ ደግሞ በመሬት ሽያጭና በቤት ግንባታ ዙሪያ ነው።

ሕዝብ ለዓመታት የኖረበትን የግል መሬቱን ተነጥቆ የመሬት ባንክ ወደሚለው የመንግሥት ይዞታ ከገባ በኋላ ሕዝብ የራሱን መሬት መልሶ ከመንግሥት እንዲገዛ፣ወይም ከኖረበት ቤት ተፈናቅሎ በነዋሪው ፍላጎትና አቅም አንጻር በተሰሩት ሳይሆን ብዙ ገንዘብ በሚጠየቅባቸውና ጥራት በጎደላቸው አደገኛ መኖሪያ ቤቶች እንዲሰገሰግ ይገደዳል። የሚጠየቀውን የገንዘብ መጠን ለመክፈል የሚችለው በጣም አነስተኛና ከመንግስት ጋር ቅርበት ያለው ወገን ብቻ ነው።ሌላው ሰፊ ሕዝብ አማራጭ ስለሌለው ከአቅሙ በላይ የሆነ አንድ አማራጭ ብቻ ይኖረዋል፣ያም አማራጭ መንግሥት ወይም ከመንግሥት ባለስልጣኖች ጋር የተያያዘ የባንክ የአገልግሎት ግዳጅ ውስጥ መግባትና ከፍለው ከማይጨርሱት ወይም ሊከፍሉት ከማይችሉት ዕዳ ውስጥ መነከር ነው።

በሌላው የሰለጠነ አገር ውስጥ ያለው የብድር አይነት የተለያየ ሲሆን የሚጠየቀውም ወለድ እንደዚያው የተለያየ ነው።ለንግድ ማስፋፊያ ለመኖሪያ ቤት ግዥና ግንባታ፣ለዕለት ዕለት ግላዊ አውሎት የሚሰጠው ብድር ወለዱ ይለያያል።ከብድሩ ሁሉ ዝቅተኛ ወለድ የሚጠየቅበት ለቤት ግዥና ግንባታ በሚሰጠው ብድር ላይ ነው።በአሁኑ ጊዜ በከበርቴ የምዕራቡ አገሮች ሕዝቡ ቤት እንዲገዛ ስለሚፈለግ ለዚህ ተግባር ለሚሰጠው ብድር የሚከፈለው ወለድ በጣም ዝቅ ያለ ሲሆን እንደ ዓመቱ ማጠርና መርዘም ከ1.5 %እስከ 3% ብቻ ነው።በኢትዮጵያ ግን ያለው የሚያስደነግጥ ነው።ለቤትም ሆነ ለሥራ ማስፋፊያ፣ለቅንጦት ዕቃ፣ ለመኪና ወይም ለሸርሽር ለሚውለው ገንዘብ ብድር የሚጠየቀው ወለድ አንድ አይነት ነው።መንግሥት ከሕዝቡ ነጥቆ ለገበያ ያወጣውን መሬቱንና ቤቱን ገቢው መጠነኛ የሆነ ደሃ እንዲገዛ ሲገደድ እንዲከፍል የሚጠየቀው መንግሥት በካሬ ሜትር በደነገገው ዋጋ ሲሆን ያንን ለመክፈል ደግሞ የባንኮችን እጅ ማየቱ የማያመልጠው  ግዴታ ነው።ያንን ግዳጅ ተቀብሎ ውል ያልፈረመ ለኖረበት ቤትና መሬት ባለቤት አይሆንም።ተነጥቆ መክፈል ለሚችል ወይም ለባለሥልጣኖች ቅርበት ላለው በልዩ አስተያየት እንዲወስደው ይደረጋል።የዚህ አይነቱ አሰራር የሚፈጥረው ትርምስና ውዝግብ  የተነሳ በቅርቡ ላፍቶ፣ሰሞኑንም በመርካቶ አካባቢ በነዋሪውና  በመንግሥት ወታደሮች የሚደገፈው የካድሬዎችና የአፍራሽ ሃይል መካከል በተደረገው ግጭት ከዘጠኝ ሰዎች በላይ ሕይወት ሲጠፋ ቁጥራቸው ያልታወቁ ሰዎች ቆስለዋል።በሌሎቹም አካባቢዎች ውጥረትና ስጋቱ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ በመሄድ ላይ ነው።ሕዝቡ በቀላሉ ከቤትና ከያዘው መሬት ላለመልቀቅ የላፍቶን ነዋሪዎች ትግል እንደምሳሌ ወስዶ በመዘጋጀት ላይ እንደሆነ የሚያበስሩ ዜናዎች መፍለቅ ጀምረዋል።የብሶቱና የቀውሱ ምክንያት የሆነው ከላይ በዝርዝር እንደተቀመጠው ዓይን ያወጣው የመንግሥት የዘረፋ መመሪያ ነው።

የዘረፋውን መጠን ለማሳየት መንግሥትና ባንኮቹ ተመሳጥረው ያወጡትን የብድርና የወለድ መጠን በሚከተለው የሰነድ ሰንጠረዥ ማየት ይቻላል።መንግሥት ሕዝብ እንዳይበዘበዝ መከላከል ሲገባው ሕግና አንቀጽ ነድፎ ለማይጠግቡ ጅቦች(ባንኮች)አጋልጦታል፤አንዳንዶቹ ባንኮችም በባለስልጣኖቹ፣በፖለቲካ ቡድኖችና ስብስቦች የሚተዳደሩና የሚመሩ ናቸው።ለምሳሌም ወጋገን፣ንብ፣አንበሳ የተባሉት ባንኮች የሕወሃትአባላትና ደጋፊዎች የተሰገሰጉበት ሲሆኑ፣አዋሽ የኦሮሞ ተወላጆች የሚቆጣጠሩት ነው። ሌሎቹም ቁጥር ስፍር የሌላቸው ባንኮች በዚሁ መልክ የተደራጁ ናቸው።እነዚህን ለመጥቀም ሲባል ነው በልማትና

ግንባታ በሚል ሽፋን ሕዝቡ ከማይችለው ዕዳ ውስጥ እንዲነከር ወይም ንብረቱን ተነጥቆ መኖሪያ ቢስ እንዲሆን የሚደረገው።ፈቃድና ካርታ የለህም ተብሎ ለዘመናት የኖረበትን ተወልዶ አድጎ እሱም ወልዶና አሳድጎ የኖረበትን ቦታ በሕገወጥነት ተፈርጆ በመነጠቅ ከሌላ ቦታ ለመጡ ለስርዓቱ ቅርበት ላላቸው መሰጠቱና ገንዘብ ላላቸው መሸጡ አግባብ ያለው አሠራር አይደለም።እርግጥ ነው ፈቃድና ካርታ ሳይኖር ቦታ መያዙ ተገቢ ነው አይባልም፣ግን በቦታው ላይ ነዋሪዎቹ በመቼ ጊዜ ሰፈሩ?ምን ያህል ዓመት ኖረዋል?በዚያን ጊዜ የመሬቱ ዋጋ ስንት ነበር?ብሎ መጠየቅና ከነዋሪዎቹ አቅም አንጻር እየታዩ እንዲከፍሉ ማድረግ በተገባ ነበር።ጥፋቱ የሕዝቡ ብቻ ሳይሆን በጊዜው የነበረው አስተዳደርና መንግሥት ጭምር ነው።ተከታትሎ ሕግን ማስከበር በተገባ ነበር።በተጨማሪም አንድ መንግሥት ሕዝቡ መጠለያ እንዲያገኝ፣የከተማም ሆነ የገጠር መሬት እንደአቅሙ እንዲኖረው የማድረግ እንጂ ሕዝብን መሬት አልባ የሚያደርግ ሕግ አውጥቶ አያስገድድም።በኢትዮጵያ ያለው መንግሥት ግን መሬትን፣ሥራን፣ትምህርትን...የመሳሰሉትን የሕዝብ መብቶች  እንደ ሸቀጥ የሚቸረችር ወይም ለወደደው የሚሰጠው ለጠላው የሚነሳው ወይም  ለፖለቲካ ሥልጣን መቆያ መሳሪያ አድርጎ የሚጠቀምበት ሆኗል።በውጭ አገር ከሚኖረውም ኢትዮጵያዊ መሃል ከድሆች ወገኖቹ እየተቀማ ለሽያጭ የሚቀርበውን ቦታ እየገዛ የወንጀሉ ተባባሪና የመንግሥት ደጋፊ የሆነው ቁጥሩ ቀላል አይደለም።ሕዝቡም በነዚህ ላይ ያለው ጥላቻ ከፍተኛ ነው።ለራስ ምቾትና ደስታ ሲሉ ሕዝብን ማፈናቀል የሚያስከትለውን አደጋ ያጤኑት ጥቂቶቹ ናቸው።

የኖሩበትን ቦታ መልሰው እንዲገዙ ከተገደዱት መካከል ለማስረጃ ያህል የሚከተለው ሰነድ ቀርቧል።በሰንጠረዡ ላይ እንደሚታየው ብድሩ ሳይከፈል ዕዴሜው ተራዝሞ ከፍተኛ ወለድ ብቻ እንዲከፈል ተደርጓል።ይህ አሰራር ደግሞ ሕዝቡን የዕድሜ ልክ ዕደኛ ከማድረጉም በላይ ለመክፈል ባይችልና ቢነጠቅ የሚያገኘው አይኖርም ፣ቢኖርም በጣም አነስተኛ ይሆናል።በዚያም ሆነ በዚህም ትርፍ የሚያግበሰብሱትና የሚጠቀሙት ሕጋዊ ሽፋን የተሰጣቸው ባንኮች ናቸው።ለሕዝብ ጥቅምና ለአገር ዕድገት የሚያስብ መንግሥት ሕዝብ በአነስተኛ ወለድ ተበድሮ ሊቋቋምበት የሚችልበትን መንገድ ወይም የመንግሥት የብድር ተቋም መፍጠር ይኖርበት ነበር።የሩቅ ጊዜ ትዝታም ቢሆን የዛሬውን አያድርገውና በዘውድ ስርዓት ጊዜ የልማት ባንክ(morgage Bank)የሚባለው ለዚህ ዓላማ ነበር የተፈጠረው።

ይህ ከዚህ በታች የሚታየው የብድር ሰነድ የተበዳሪው ስምና አድራሻ የሰፈረበትን የመጀመሪያ ገጽ ለደህንነት ሲባል በመቀነስ  በሕዝቡ ትከሻ ላይ የሚጫነውን የዕዳ ክምር እንድትረዱት ከዋናው ሰነድ ኮፒ ተደርጎ የቀረበ ነው።እንደሚታየው ለሃምሳ አራት ሽህ ብር(54,000) ብድር ለአርባ ዓመት በ9.5 % ወለድ ሂሳብ(በየጊዜው ሊለዋወጥና ሊያድግ ይችላል)ያለውድ በግድ የተፈረመ ውል ነው።በውሉ መሰረት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚከፈለው የወለድ ልክ ከ150 ሽህ(150,000)በላይ ይሆናል።ዋናው ሲጨመርበት ደግሞ ከ200ሽህ(200,000) ቢበልጥ እንጂ አያንስም።ዕዳው የሚወሰነው የመሬቱ ባለቤት በሆነው መንግሥት በቦታው ላይ ባስቀመጠው የካሬ ሜትር ዋጋ መጠን ነው።ያ ደግሞ ከሕዝቡ አቅምና ከአገሪቱ እድገት ደረጃ ጋር የተመጣጠነ አይደለም።የመንግሥት ዓላማው ገንዘብ ማግበስበሱ እንጂ የሕዝቡ ደህንነትና ሰላማዊ ኑሮ አይደለም።በመሃል ከተማው ሳይሆን በከተማ ጠርዝ የሚገኝ ቦታ ዋጋ በካሬ ሜትር ከአራት ሽህ ብር በላይ በመንግሥት የመሬት ባንኩ ይጠየቅበታል። ታዲያ አንድ ደሃ ሰራተኛ ወይም ሥራ አጥ እንዴት አድርጎ የቤትና የራሱ ቦታ ባለቤት ሊሆን ይችላል?። አንድ የቀን ሰራተኛ በወር ግፋቢል 700 ብር የሚያገኝ ባለቤተሰብ የተወለደበትንና የሚኖርበትን ቦታ ተነጥቆ እንዲገዛ ሲገደድና ዋጋውም በካሬሜትር 4ሽህ ብር ከሆነና ቦታው 150 ካሬ ሜትር ከሆነ እንዴት 600ሽህ(600,000) ብር ከፍሎ  የራሱን ቦታ አስከብሮ  ሊኖር ይችላል? ይበደርስ ቢባል ከየት አምጥቶ የባንክ ዕዳ ሊከፍል ይችላል?ያለው ዕድል ቤቱ በአፍራሽ ቡድን ተደምስሶ የመንገድ ላይ ተዳዳሪ ወይም ከሚያገኘው የወር ገቢ ሲሶውን ለደባል የቤት ኪራይ እየከፈለ መኖር ነው።

እንደዚህ ሕዝቡን ለችግርና ለመከራ የዳረገ መንግሥትና ስርዓትስ ለምንና እስከመቼስ በስልጣን ላይ ሊኖር ይገባዋል?

በሰንጠረዡ በመጀመሪያው መስመር ላይ ለ54ሽህ(54,000) ብር ብድር ከሃያ ዓመት ክፍያ በኋላ ቀሪውና በየዓመቱ የሚከፈለው ማቃለያና ወለድ ቁልጭ ብሎ ይታያል፤በመጀመሪያውና ከዚህ ጋር ባልቀረበው ገጽ ላይ በሃያ ዓመት ውስጥ የተቃለለው ገንዘብ ትንሽ ሲሆን የተከፈለው ወለድና ቀሪው ዕዳ

